# “ሲሮጡ ፡ የታጠቁት ፣ ሲሮጡ ፡ ይፈታል።”

<u>ለቅንጅት ፡ መልእክተኞች ፡ ማሳሰቢያ ፤</u>

ከሞገስ ፡ ታምሩ ፤ ካናዳ ።

ለአቶ ፡ ብርሃነ ፡ መዋና ፡ ለሌሎቹም ፡ ተባባሪዎች ፡ የማሳስበው ፣ ወገንታዊ ፡ ቡድን ፡ ከመፍጠር ፡ ይልቅ ፡ የሁሉንም ፡ ቅንጅት ፡ መልእክተኞች ፡ ተባብረው ፡ የሚሠሩበትን ፡ ዘዴ ፡ ማዘጋጀቱ ፡ ይሻላል ። የአሁኑ ፡ ሁኔታ ፡ ግን ፡ ችግር ፡ ፈጥሯል ። ይኸውም ፡ ከአዲስ ፡ አበባ ፡ ተልከው ፡ የመጡትን ፡ መልእክተኞች ፡ ከአቀባበሉ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ጀምሮ ፡ የለያያቸው ፡ መሆኑ ፡ ሲነገር ፡ የሰማነው ፡ አሉቧልታ ፡ በጣም ፡ አሳዛኝ ፡ ነው ። አባቶች ፡ በቀደምት ፡ ዘመናት ፡ ትረካ ፡ ይናገሩ ፡ የነበረው ፡ በመጀመሪያ ፡ ከላይ ፡ ለተጠቀሰው ፡ አባሪ ፦ “የቸኰለ ፡ አፍስሶ ፡ ለቀመ ።” የተባለው ፡ ጥቅስ ፡ የሚያሳስበው ፡ ሳትቸኩሉ ፡ ሥሩ ፡ ለማለትና ፡ ወደ ፡ ዋሽንግተን ፡ የመጡትን፡ የቅንጅት ፡ መልእክተኞች ፡ ከዋናው ፡ መሪ ፡ ተለይተው ፡ ያደረጉትና ፡ የወሰዱት ፡ እርምጃ ፡ አግባብ ፡ አለመሆኑን ፡ ያመለክታል ። መልእክተኞቹም ፡ ከአዲስ ፡ አበባ ፡ ወደ ፡ ሰሜን ፡ አሜሪካ ፡ ሲላኩ ፣ ከአመራሩ ፡ አባሎችና ፡ ከደጋፊው ፡ ሕዝብ ፡ የአደራ ፡ ቃል ፡ ተቀብለዋል ። እሱም ፡ በኢዮጵያ ፡ ያለውን ፡ ሁኔታ ፡ እንዲያስረዱ ። አሜሪካ ፡ በሚኖሩት ፡ የቅንጅት ፡ አባሎችና ፡ ደጋፊዎች ፡ መካከል ፡ የሐሣብ ፡ መለያየት ፡ ተፈጥሮአል ፡ የተባለውን ፡ አስወግደው ፡ ለማስማማት ፡ እንጂ ፣ ከዋናው ፡ መሪ ፡ በመለየት ፡ አዲስ ፡ ቡድን ፡ ፈጥሮ ፡ እንዲነጋገሩ ፡ አልነበረም ። እንደዚሁም ፣ በኢትዮጵያ ፡ የሚገኘው ፡ የቅንጅት ፡ ድጋፍ ፡ ሰጪው ፡ ኃይል ፤ ከኢንጂኔር ፡ ኃይሉ ፡ ሻውል ፡ በመለየት፦ ዶ/ር ፡ ብርሃኑ ፡ ነጋ ፣ ወ/ት ፡ ብርቱካን ሚደቅሳና ፡ አጃቢዎቻቸው፡ ከዓላማው ፡ ውጭ ፡ በየጊዜው ፡



የሰጡትን ፡ መግለጫና ፡ አስተያየት ፡ እንዴት ፡ አድርጎ ፡ ይመለከተው ፡ ይመስላችኋል? ።

ኢንጂኔር ፡ ኃይሉ ፡ ሻውልን ፡ የቅንጅት፡ አባላትና ፡ ሕዝቡም ፡ የመረጠው ፡ ጠንካራ ፡ መሪ ፡ መሆኑን፡ በማወቅ ፡ ነው። እናንተም ፡ እዚህ ፡ የምትገኙት፡ አባሎች ፡ ጠንካራና ፡ ብርቱ ፡ መሪ ፡ መሆኑን ፡ ሳትክዱ ፡ ታውቃላችሁ። ታዲያ! ፡ ጠንካራና ፡ ለአመነበት፡ ዓላማ ፡ የሚቆም፡ መሪ ፡ መወደድ ፡ ይገባዋል ፡ እንጂ ፡ ሌላ ፡ ስሜት ፡ በአባሎቹ ፡ ዘንድ ፡ ሊፈጠር ፡ ይችላል ፡ ወይ? ። እንዲያውም ፡ በኅብረት ፡ መሥራቱን ፡ ያጠናክረዋል ፡ ብየ ፡ አምናለሁ ።

ከዚህም፡ ተጨማሪ ፡ ኢንጂኔር ፡ ኃይሉ ፡ ሻውል ፡ በዕድሜው ፡ ታላቅነት ፣ በረጅም ፡ አመታት ፡ ያገኘው ፡ የሥራ ፡ ልምድ ፣ ለኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ የሚበጀውን ፡ ለይቶ ፡ የሚያውቅ ፡ ነው ። ለአገሪቱ ፡ ዕድገት ፡ ሰላምና ፡ ቀና ፡ አስተዳደር ፡ ማስፈለጉን ፡ በማሰብ ፡ የቆመለት ፡ ዓላማውና ፡ የናንተም ፡ አቋም፡ በዚሁ ፡ ሁኔታ ፡ የተመሠረተ ፡ በመሆኑ ፣ ሁሉንም ፡ ወገን ፡ በቅን ፡ አስተያየት ፡ ተመልከቱት ። የመከፋፈያ ፡ አነጋገር ፡ ዘይቤውን ፡ ሰርዛችሁና ፡ ለዘለቄታው ፡ አመራር ፡ የሚያሰጋውን ፡ ወደጐን ፡ ትታችሁ ፡ የቅንጅት ፡ ደጋፊ ፡ ኃይል ፡ በሰጣችሁ ፡ አደራ ፡ ላይ ፡ አተኩሩ ። የድርጅቱን ፡ አመራር ፡ ሥርዓት ፡ ለማስያዝ ፡ የሚቻልበትን ፡ ለመቀየስ ፡ መተባበራችሁ፡ ዋናው ፡ ጥያቄ ፡ ነው ። ሌላው ፡ መነታርኩና ፡ በሐሣብ ፡ መለያየቱ ፡ የሚጠቅመው ፡ ለከፋፋዩ ፡ ገዢ ፡ መሆኑን ፡ ሳትዘነጉና ፡ በሩን ፡ ክፍት ፡ አድርጋችሁ ፡ በሌላ ፡ ዕቅድ ፡ መሽቀዳደማችሁ ፡ ያሳዝናልና ፡ አስቡበት ። እንደገናም ፡ ንትርኩና ፡ ወገን ፡ መለየቱ ፡ የሚጠቅመው ፡ ኢትዮጵያን ፡ በዲሞክራሲ ፡ ስም ፡ አስተዳድራለሁ ፡ ለሚለው ፡ መንግሥት ፡ ብቻ ፡ መሆኑን ፡ መዘንጋት ፡ የለባችሁም ።

ያም ፡ ሆነ ፡ ይህ ፣ ኢንጂኔር ፡ ኃይሉ ፡ ሻውል ፡ በአቋሙ ፡ ጠንካራ ፣ ለአገሩ ፡ የሚጠቅመውን ፡ የሚያውቅና ፡ ቸል ፡ ሳይል ፡ ራሱን ፡ የሚያጋፍጥ ፡ ነው ። ለዚህም ፡ ማስረጃ ፡ በደርግ፡ አገዛዝ ፡ የሚኒስትርነት፡ ሥልጣኑን ፡ ጥይት ፡ በረከሰበት ፡ ወቅት ፡ ለሕይወቱ ፡ ሳይሣሣ ፡ ያውላችሁ ፡ ብሎ ፡ ራሱን ፡ አግልሏል ። ችግር ፡ ደርሶበትም ፡ የተቋቋመ ፡ አስተዋይ ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ መሆኑንና ፡ በቆራጥነት ፡ የወሰደው ፡ ውሳኔ ፡ የማይረሳ ፡ ነው ። ራሱንና ፡ ቤተ ፡ ሰቡን ፡ ያለ ፡ ችግር ፡ ማስተዳደር ፡ የሚችል ። ጥቅም ፡ ፈላጊና ፡ ለሥልጣን ፡ ጉጉት ፡ የሌለው ። ፈላጭ ፡ ቆራጭነትን ፡ የሚያወግዝ ፡ የጠራ ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ መሆኑ ፡ አያጠራጥርም ። ስለዚህ ፡ አጥብቄ ፡ ለዶ/ር ፡ ብርሃኑ ፡ ነጋ ፣ ለወ/ት፡ ብርቱካን ፡ ሚደቅሳ ፣ ለዶ/ር ፡ ኃይሉ ፡ አርኣያና ፡ ለሌሎቹም ፡ አባሎች ፡ ለማሳሰብ ፡ የምወደው ፦ ኢትዮጵያ ፡ ሰላምና ፡ ጸጥታ ፡ እንድታገኝ ፣ ሕዝቧ ፡ ከዕለት ፡ ኑሮው ፡ ጀምሮ ፡ በመንገላታቱ ፡ ከችግርና ፡ ከጭቆና ፡ አገዛዝ ፡ የሚላቀቅበትን ፣ በጥይት ፡ የተደበደቡትን ፡ ወገኖቻችንን ፡ በማስታወስ ፡ ከኢንጂኔር ፡ ኃይሉ ፡ ሻውል ፡ ጋር ፡ ተባበሩ ። የቅንጅትን ፡ የፖለቲካ ፣ ኢኮኖሚ ፣ ሶሻልና ፡ አስተዳደር ፡ ዕቅዳችሁን ፡ በተግባር ፡ ለመፈጸም ፡ የምትችሉት ፤ አንድነታችሁን ፡ አጠናክራችሁ ፡ ስትገኙ ፡ ብቻ ፡ ነው ። እንግዲህ ፡ የምጠይቃችሁ ፡ ኅብረታችሁን ፡ ከመሪያችሁ ፡ ጋር ፡ ታጠናክሩ ፡ ዘንድ ፡ በጥብቅ ፡ አደራዬን ፡ አስተላልፋለሁ ። ኢትዮጵያ ፡ እጆቿን ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ስትዘረጋ ፡ አብረናት ፡ እንዘርጋ ።

**ኢትዮጵያና ፡ ቅንጅት ፡ ያሸንፋልሉ ። በኃይሉ ፡ ሻውል ፡ መሪነት ፡ ወደፊት!!!! አመሰግናለሁ። ጠንካራ ፡ ልቦና ፡ ይስጠን። አሜን ።**

መስከረም ፡ ፳፬ ፡ ፪፻፯ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ። **10/04/07.**